# በኖርዌይ የኢሕአፓ የሴቶች ኮሚቴ አባላትና ደጋፊዎች የዘንድሮውን ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በደማቅ ሁኔታ አክብረው ዋሉ




በኖርዌይ የኢሕአፓ የሴቶች ኮሚቴ አባላትና ደጋፊዎች ትላንት (የካቲት 29 ቀን 2004 ዓ. ም.) የተከበረውን ዓለም አቀፍ የሴትች ቀን በደማቅ ሁኔታ አክብረው ውለዋል። በወያኔ ተይዛ ደብዛዋ የጠፋው ጓዳቸውን የአበራሽ በርታን ፎቶ፣ ዘረኛው የወያኔ ሥርአት በሴቶች ላይ እየደረሰ ያለውን አሰቃቂ ሁኔታና ሕዝባዊ ስሜትን ገላጭ የሆኑ የተለያዩ ወቅታዊ መፈክሮችን በማንገብ ነበር




ለበዓሉ የወጡት።

በወቅቱም በራሪ ወረቀቶችን ለሕዝቡ በማደል፣ ወቅታዊውን የአገራችንን ሁኔታና ዘርፈ ብዙ የሆነውን የወያኔንን አስከፊ ባህሪያትም አጋልጠዋል።




በተጨማሪም የኖርዌይ መንግስት የሰውን ልጅ ያህል ክቡር ነገር በገንዘብ በመለወጥ፣ ከዚህ ዘረኛና አጥፊ ቡድን ጋር የደረሰበትን የመሸጥ ስምምነት ማለትም ኢትዮጵያውያን ስደተኞን አስገድዶ ወደ ኢትዮጵያ የመመለስ ጉዳይንም ዴሞክራትና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ሀይሎች እንዲያወግዙት፣ ኢትዮጵያውን ስደተኞችም ጉዳያቸው በአግባቡ እንዲታይ፣ የመኖርና የመሥራት መብታቸው እንዲከበርላቸውም የሚግልፁ መፈክሮችን በማሰማትና በረሪ ወርቀቶችን ለሕዝቡ በማደል በዓሉን በደመቀ ሁኔታ አክብረዋል ።




Kvinner sier
stopp
forverring av


STANDS FOR
THE
OF